አፍሪካ ቲቪ

ከታላቁ ቁርአን
የመጨረሻዎቹ
‹‹የሶስቱ ክፍሎች››
ማብራሪያ
ዋና ዋቢ
ዙብደቱ ተፍሲር



# አፍሪካ አካዳሚ

## AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአቂዳ ትምህርት 2

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

## ሁለተኛው አለም አቀፍ የርቀት ትምህርት መሪ ቃል
## “ትክክለኛው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው”




“አላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው ፡፡”

**ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ**
**የአፍሪካ አካዳሚ**
**የርቀት ትምህርት**
**1441 ሒጅሪያ/2020**

# በነቢያት ማመን ማለት ምን ማለት ነው?

አላህ (ሱ.ወ) ለተለያዩ ህዝቦች ወደርሱ የሚጠሩና እሱ የብቸኛ አምልኮት ባለቤት መሆኑን እና ከሱ ሌላ ማንም ሊመለክ የማይገባው መሆኑን የሚያስተምሩ አማኞችና እውነተኞች የተከበሩ ቀናኢዎች ፈሪሃ አላህ ያደረባቸውን ነቢያትን ልኳል፡፡

እነሱም የተላኩበትን በትክክል አድርሰዋል፡፡ እነሱም ከፍጡሩ ሁሉ ምርጦች ናቸው፡፡

በአላህ (ሱ.ወ) ከማጋራትም ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሞታቸው ድረስ የፀዱ ናቸው ብሎ በቁርጠኝነት ማመን ነው፡፡

## በመልእክተኞች ማመን

ሰዎች መጀመሪያ ላይ በንጹሕ ተፈጥሯቸው በትክክለኛው መንገድ ላይ የነበሩ ሲሆን፣በኋላ ተለያዩና መሐይምነት ከገባ ቡኋላ እነሱም ያስተምሯቸውና ያስጠነቅቋቸው ዘንድ አላህ መልክተኞቹን ላከላቸው።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

‹‹እርሱ ያ በመሃይሞች ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርአንን)፣በነርሱ ላይ የሚያነብላቸው፣(ከማጋራት) የሚያጠራቸውም፣መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸው የኾነን መልክተኛ (ሙሐመድን) ከነሱው ውስጥ የላከ ነው፤እነርሱም ከርሱ በፊት በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበሩ።››[አል ጁሙዓ፡2]

## በቂያማ ቀን የሚኖሩት የሸፈዓ /የሽምግልና/ምልጃ/ አይነቶች ስንት ናቸው?

የሽምግልና አይነቶች ብዙ ናቸው፡፡

### አንደኛውና ዋናው - <u>ታላቁ ሽምግልና</u> የሚባለው ነው፡፡

እርሱም ሰዎች ሀምሳ ሺህ አመት ሙሉ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ሲጠባበቁ ከቆዩ በኋላ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጌታቸውን ለምነው ለውሳኔ የሚያበቁበት የሽምግልና ሂደት ነው፡፡

ይህ ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ብቻ የተሰጠ ማዕረግ ነው፡፡ ይህም ያ! አላህ ቃል የገባላቸው ምስጉኑ ቦታ የተባለው ነው፡፡

**ሁለተኛው ሽምግልና** - የጀነትን በር ለማስከፈት የሚደረገው ሽምግልና ሲሆን ለዚህም የመጀመሪያ ጠያቂው ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ናቸው፡፡ ከሕዝቦችም ሁሉ የመጀመሪያ ገቢዎች የነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኡመቶች ናቸው፡፡

**ሦስተኛው ሽምግልና** - እሳት እንዲገቡ የተወሰነባቸውን ሰዎች እሳት እንዳይገቡ ለመለመን የሚደረገው ሽምግልና ነው፡፡

**አራተኛው ሽምግልና**- ከሙስሊሞች መካከል በወንጀል ወደ እሳት ገብተው ያሉትን ሰዎች ከእሳት ለማስወጣት የሚደረገው ሽምግልና ነው፡፡

**አምስተኛው ሽምግልና** - ጀነት የገቡ ሰዎች በጀነት ውስጥ የደረጃ እድገትን እንዲሰጣቸው የሚደረገው ሽምግልና ነው፡፡ በነዚህ በመጨረሻ በተወሰቱ በሶስቶቹ የሽምግልና አይነቶች ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ግንባር ቀደም ቢሆኑም ለሳቸው ብቻ የተለየ አይደለም፡፡ ከሳቸው ቀጥሎ ነቢያት፤ መላኢኮች፤ ሳሊህ ሰዎችና የኢስላም ሰማዕታት /ሸሂዶች/ ይከተላሉ፡፡

**ስድስተኛው ሽምግልና** - ሰዎች ያለምንም ጥያቄና ምርመራ ጀነት እንዲገቡ የሚደረገው የሽምግልና ሂደት ነው፡፡

**ሰባተኛው ሽምግልና** - አላህ የአንዳንድ ከሃዲዎችን ቅጣት እንዲያቃልል የሚደረገው ሽምግልና ነው፡፡ ይህም ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የአጎታቸው የአቡጣሊብን ቅጣት ለማቃለል ብቻ የሚያደርጉት በመሆኑ ለእሳቸው ብቻ የተለየ ነው፡፡

**ስምንተኛው** ፡- ከዚያም አላህ (ﷻ) ተውሒድ ኖሮዋቸው የሞቱና ወደ እሳት ገብተው የነበሩ ቁጥራቸውን እሱ ብቻ የሚያውቃቸውን ብዙ ሰዎችን ያለምንም ሽምግልና /አማላጅ/ ያወጣና ጀነት ያስገባቸዋል፡፡

## ተወሱል/ ወደ አላህ መቃረብ/መጠጋት/ ስንት ክፍል አለው?

ተወሱል ሁለት ክፍል አለው፡፡

### አንደኛው ክፍል የሚፈቀደው

በአላህ (ﷺ) ሰሞችና ባህሪያት መወሰል/ወደ አላህ መቃረብ/፤

በራስ መልካም ስራ መወሰል ሲሆን፤ ምሳሌውም የነዚያ ሶስት የዋሻ ሰዎችን ታሪክን ይመስል ነው፡፡

ጉዳዩን በሚሰማና በህይወት ባለ ከአላህ (ﷻ) ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ተስፋ በሚጣልበት ሙስሊም ሷሊህ/በጎ ሰው/ ዱዓ መወሰል ናቸው፡፡

### ሁለተኛው የተወሱል አይነት የሚከለከለው ተወሱል

በነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ወይም በወሊይ ክብርና ግርማ ሞገስ መወሰል ነው፡፡

በነቢይ ወይም በወሊይ ምሎ ጌታውን መለመን ነው፡፡ አይፈቀዱም፡፡